29ኛ ዓመት ቁጥር 29
29th Year No. 29

ባሕር ዳር ግንቦት 29 ቀን 2017 ዓ.ም
Bahir Dar, June 6, 2025

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG
of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 1803.20 ብር
Unit Price Birr 1803.20

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፲፯ ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕል ፍርድ ቤቶችን ማቋቋሚያና እውቅና መስጫ አዋጅ

<u>Content</u>

Proclamation No 298/2025
The Amhara National Regional State Custumory Courts Establishement and Recognition Proclamation

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፲፯ ዓ.ም
## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባሕል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና እውቅና ለመስጠት የወጣ አዋጅ

የክልሉ መንግሥት መሠረታዊና ሰብዓዊ መብቶችን፣ ዲሞክራሲን እና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባሕሎች እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ ለመርዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፤

ጉዳያቸው በባሕላዊ ሥርዓት መሠረት እንዲታይላቸው የሚፈልጉ ተከራካሪዎች የክልሉ ሕገ መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት በሚቋቋሙና ዕውቅና በሚሰጣቸው ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች መስተናገድ እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ፤

## Proclamation No 298/2025
## A proclamation Issued for the Establishment and Recognition of the Amhara Naional Regional State Customary Courts

WHEREAS, the regional government has responsibility to support the development and preservation of customs which does not contradict fundamental human rights, democratic principles, and the constitution;

WHEREAS, it is stipulated that parties seeking to resolve their disputes may do so in a customary court to be established and recognized in accordance with the region's constitution;

ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ለማኅበረሰቡ በቀላል ቋንቋ ለመግባባት የሚያስችሉት፣ እውነት በማውጣትና ፍትሕን በማስፈን ውጤታማ የሆኑ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ተደራሽ ከመሆናቸውም በላይ በየአካባቢው የሚገኘው ማኅበረ-ሰብ የፍትሕ አገልግሎት እንዲያገኝ ቀለል ያለ ሥነ-ሥርዓት የሚከተሉ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ በመሆኑ፤

በክልሉ መደበኛ እና ባሕላዊ ፍርድ ቤት መሀል የተሻለ መናበብ እና መጣጣም የፍትሕ ውጤታማነትን ለማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ (፩) ድንጋጌ ሥር በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ **"የአማራ ክልል የባሕል ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም እና እውቅና ለመስጠት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፲፯ ዓ.ም"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ **"ሕገ መንግሥት"** ማለ የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ነው::

፪/ **"መንግሥት"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው::

፫/ **"ክልል"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ነው::



WHEREAS, custumory courts follow simplified procedures and help to promoting sustainable peace so that the society found at each area get justice besides their enabling the society easily communicate through familiar language, efficiently uncovering the truth, and providing cost-effective and accessible means of justice;

WHEREAS, ensuring coordination and compatibility between regular courts and customary courts in the region is vital for enhancing the effectiveness of justice;

NOW, THEREFORE, the Amhara National Region Council, in accordance with Article 49 (3) (1) of the Revised Amhara Regional State Constitution, hereby proclaimed this proclamation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "**The Amhara Region Customary Courts Establishment and Recognition Proclamation No 298/2025.**"

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1/ "**Constitution**" means the Revised Amhara National Regional State Constitution.

2/ "**Government**" means the Amhara National Regional State Government.

3/ "**Region**" means the Amhara National Region.

፬/ **"ባሕላዊ ፍርድ ቤት"** ማለት በባሕላዊ ሕጎች ላይ ተመርኩዞ እንዲሠራ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ወይም እውቅና የተሰጠው አማራጭ ያለመግባባት መፍቻ ሥርዓት ነው፡፡

፭/ **"መደበኛ ፍርድ ቤት"** ማለት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተቋቋመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡

፮/ **"ባሕላዊ ሕግ"** ማለት የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሠራበት አካባቢ የሚገኝ የባሕል ሕግ ሆኖ ሕገ መንግሥትን፣ ሞራልንና የተፈጥሮ ፍትሕን የማይቃረን ሕግ ነው፡፡

፯/ **"ሽማግሌ"** ማለት በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራትን ለማከናወን በባሕል ፍርድ ቤት የተሾመ (የሚያገለግል) ሆኖ እንደየአካባቢው የባሕል ሕግ በተለያዩ ስያሜዎች ሊጠራ ይችላል፡፡

፰/ **"ባለጉዳይ"** ማለት በባሕላዊ ፍርድ ቤት ውስጥ ተከራካሪ፣ ተሸማጋይ፣ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ይግባኝ ባይ፣ መልስ ሰጪ ወይም እንደአስፈላጊነቱ አስረጂ ወይም አስፈጻሚ እና ወኪል የሆነ ሰው/አካል ነው፡፡

፱/ **"ፀሐፊ"** ማለት የባሕል ፍርድ ቤትን እንዲያግዝ የሚመደብ ባለሙያ ነው፡፡

፲/ **"ኮሚቴ"** ማለት ሽማግሌዎችን ለማስመረጥ በወረዳ ወይም በቀበሌ የሚቋቋም አካል ነው፡፡

፲፩/ **"አጥጋቢ ምክንያት"** ማለት የባሕል ፍርድ ቤት የሚሠራበት አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ በባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌዎች እንደ አሳማኝ ምክንያት የሚወሰድ የትኛውንም ምክንያት ነው፡፡



4/ **"Customary Court"** means an alternative dispute resolution system established and recognized by this proclamation to work based on customary laws.

5/ **"Formal Courts"** means the Supreme Court, High Courts and Wereda Courts established in accordance with the Revised Regional State Constitution.

6/ **"Customary Law"** means the customary law that applies in the specific locality where the customary court is situated, provided it is not in conflict with the constitution, public morality, or natural justice.

7/ **"Elders"** means a person selected and assigned to customary courts to discharge the powers and functions granted by this proclamation and they may also be referred to by different names, depending on local customary laws.

8/ **"Party"** means anyone who is a litigant, disputing party, plaintiff, defendant, appellant, respondent, or as the case may be, witness or executor and representative in a customary court.

9/ **"Secretary"** means an expert assigned to assist elders of a customary court.

10/ **"Committee"** an organ to be organized by 'Wereda' or 'Kebele' to facilitate the selection of elders.

11/ **"Satisfactory Reason"** means any reason that elders of a customary court deem sufficient, considering the unique circumstances of the specific locality in which the court operates.

፲፪/ "ሰብሳቢ" ማለት የባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆኖ በዚህ አዋጅ ተጨማሪ ሥራዎች እና ኃላፊነቶች የተሰጡት ሰው ነው፡፡

፲፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፡፡

፲፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ ጉዳዩ በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲታይለት ፈቃደኝነቱን በሰጠ ሰው ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሚመለከታቸው ጉዳይ ላይ በዚህ አዋጅ በተጠቀሱት የተለያዩ አካላት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የባሕላዊ ፍርድ ቤት ዓላማ እና መሠረታዊ መርሆዎች

## ፬. የባሕል ፍርድ ቤት ዓላማ

የባሕል ፍርድ ቤት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የክልሉ ማኅበረሰብ የባሕል ሕግ እና እሴቶቹን መሠረት አድርጎ አለመግባባትን እንዲፈታ ማድረግ፤

፪/ የባሕል ሕግ ላይ የተመሠረተ፣ እውነት እና ፍትሕን በማስፈን ረገድ የተሻለ የተከራካሪ ወገኖችን ማኅበራዊ ግንኙነት ማጠናከር የሚችል የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓትን ሥራ ላይ በማዋል የዜጎች ሰብዓዊ መብቶችና የሕግ የበላይነት እንዲከበር አስተዋፅኦ ማድረግ፤

፫/ ለክልሉ ማኅበረሰብ ተደራሽ የሆነ፣ ወጪ ቆጣቢና ቀለል ያለ ሥነ ሥርዓትን የሚከተል የፍትሕ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤

12/ "**Chairperson**" means an assigned elder of a customary court entrusted with additional duties and responsibilities provided in this proclamation.

13/ "**Person**" means any natural or legal person.

14/ Any expression in the masculine gender shall also include to the feminine gender.

## 3. Scope of Application

1/ This proclamation shall be applicable to any person who gives his consent to the resolution of his case in accordance with this proclamation.

2/ Without prejudice to the provision under Sub-article (1) of this Article, relevant provisions of this proclamation shall be applicable to different bodies stated in this proclamation.

## PART TWO

## OBJECTIVES AND FUNDAMENTAL PRINCIPLES OF CUSTOMARY COURTS

## 4. Objectives of the Customary Court

The customary court shall have the following objectives:

1/ Enabling disputes to be solved based on customary laws and values of the regional society;

2/ Contributing to the respect for human rights and the rule of law by dispensing justice based on customary law that is better in fact finding and prevalence of justice, and strengthen the social relations of the disputants;

3/ Making the people of the region get access to justice that are affordable and low cost with simplified procedures;

፬/ የባለቤትነት ስሜት የተረጋገጠበትና ለአማራ ባሕል፣ እሴትና ቋንቋ እድገት አስተዋፅኦ የሚያደርግ የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት መፍጠር።

## ፭. መሠረታዊ መርሆች

የባሕላዊ ፍርድ ቤት መቋቋም፣ እውቅና አሰጣጥ እና አሠራር በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡-

፩/ በፈቃድ ላይ የተመሠረተ እና አማራጭ ስለመሆናቸው፤

ሀ) ባሕላዊ ፍርድ ቤት እንደ አማራጭ የግጭት እና አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች ሆነው ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን ያገለግላሉ፤

ለ) ማንም ሰው ካለፈቃዱ በባሕላዊ ፍርድ ቤት ሊዳኝ አይችልም።

፪/ ባሕላዊ ሥርዓቱ ላይ ጉዳት ያለማድረስ፤

በዚህ አዋጅ የተመከለቱ አስገዳጅ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የባሕላዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ እና እውቅና መስጫ ሕግ የባሕላዊ ተቋማትን እና አሠራሮችን ተዓማኒነት እና ባሕላዊ እሴቶችን ባስጠበቀ መልኩ መመስረት ይኖርባቸዋል።

፫/ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ከሰብዓዊ መብት ጥበቃዎች አንፃር የሚከተሉት ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ) በባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ሥነ ሥርዓቶች በሙሉ የባለጉዳይ ወገኖችን ሰብዓዊ መብት ያከበሩ መሆን አለባቸው፤

ለ) ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የሰዎችን ማኅበራዊ ሁኔታ፣ ዘር፣ ብሔር፣ ዜግነት፣ ማኅበራዊ መገኛ፣ የቆዳ ቀለም፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ አሳቤ፣ ሀብት፣ ትውልድ፣ አካል ጉዳት ወይም ሌላ ደረጃ ላይ ከተመሠረተ አድልኦ ነፃ በሆነ መልኩ መዳኘት እና አገልግሎት መስጠት አለባቸው፤

ሐ) ሴቶች እና ወንዶች በባሕላዊ ፍርድ ቤት በእኩልነት መስተናገድ አለባቸው፤



4/ Creating a legal and justice system that ensured sense of ownership and contribute for development of the Amhara culture, value and language.

## 5. Fundamental Principles

The establishment of customary courts, recognition and operating procedures shall be governed by the following principles:

1/ Being based on consent and whether they are alternatives:

A) Customary courts shall operate alongside regular courts and serve as alternative dispute resolution mechanisms;

B) No one shall be judged by a customary court without his free consent.

2/ Not harming on customary system:

Without prejudice to the mandatory requirements referred under this proclamation, the establishment and recognition of customary court law shall be based on the observance of trust worthiness of customary institutions operations and cultural values.

3/ From observance of human rights perspective, customary courts are obliged the following:

A) All procedures implemented in the customary court shall respect human rights of the parties in the dispute;

B) Customary courts shall provide their judgement and service free from discrimination based on social status, race, ethnicity, nationality, social location, color, language, religion, political or other thoughts, wealth, place of birth, physical impairement or any other status.

C) Men and women shall be equally treated In the customary court;

መ) ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የሕፃናትን የቀደምትነት ጥቅም የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው፤

ሠ) ወደ ባሕላዊ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ባለጉዳይ ወገኖች አስተርጓሚ ይዘው የመቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

ረ) በባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የሚተላለፉ የቅጣት ውሳኔዎች አካላዊ ቅጣትን ጨምሮ ኢሰብዓዊ፣ ጭካኔን የተሞላ ወይም አዋራጅና ክብረ ነክ መሆን የለባቸውም፤

ሰ) በፍርድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ሂደት ወቅት በባሕላዊ ፍርድ ቤት የተፈፀመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይግባኝ የመጠየቂያ በቂ ምክንያት መሆን ይችላሉ።

፬/ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ከመሆን አንጻር፦

ሀ) ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ማኅበረሰቡ በሚገኝበት እና አገልግሎት ተደራሽ በሚሆንበት አግባብ እንዲደራጁ እና እውቅና እንዲሰጣቸው መደረግ አለበት፤

ለ) ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙበት እና የሚሠሩበት ሕግ ተገማች እና በቀላሉ ሊገኝ የሚችል (በማኅበረሰቡ እውቅና ያለው) መሆን ይገባዋል።

## ክፍል ሶስት

## የባሕል ፍርድ ቤት ስለማቋቋም፣ እውቅና መስጠት፣ አደረጃጀት እና ሥልጣን

### ፮. የባሕል ፍርድ ቤቶች ማቋቋምና እውቅና ስለመስጠት

፩/ የባሕል ሕግን መሠረት አድርገው የሚሠሩ የአማራ ክልል የባሕል ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።



D) Customary courts shall respect priority rights of children;

E) Parties coming to customary court have the right to bring their own language translator;

F) Decisions of customary courts, including physical penalties, shall not be inhuman, degrading, full of cruelty or humiliate and violate dignity;

G) Human rights violations in the decision-making process of customary courts shall be sufficient grounds for appeal.

4/ Regarding accessibility to the society:

A) Customary courts shall be established and recognized in a manner ensuring accessibility and are located within the communities they serve;

B) The establishment of cutomary courts and laws applied in customary courts shall be predictable and easily accessible (recognized by the community).

## PART THREE

## CUSTOMARY COURTS ESTABLISHMENT, RECOGNITION, STRUCTURE AND POWER

### 6. Establishment and Recognition of Customary Courts

The Amhara Region Customary Courts operating on the basis of customary laws are hereby established by this proclamation.

፪/ የባሕል ሕግን መሠረት አድርጎ አለመግባባትን የሚፈቱ የባሕል ፍርድ ቤት አደረጃጀት ያላቸው የማኅበረሰብተቋማት ዕውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም በባሕል ሕግ መሠረት አለመግባባትን የሚፈታ ማንኛውንም የማኅበረሰብ ተቋማት በተለመደዉ ሁኔታ ከመሥራት የሚከለክሉ አይሆኑም፡፡

## ፯. የባሕል ፍርድ ቤት አደረጃጀት

፩/ የባሕል ፍርድ ቤቶች አደረጃት በየብሔረሰቡ ከተቀመጡ የባሕል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት ላይ የተመሠረተ ሆኖ በቀበሌ ወይም በወረዳ የሚመለከተው አደረጃጀት ይኖረዋ፡-

ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ የባሕል ፍርድ ቤት እና

ለ) የይግባኝ ሰሚ የባሕል ፍርድ ቤት፡፡

፪/ የባሕል ፍርድ ቤት የሚከተሉት አካላት ይኖራቸዋል፡-

ሀ) የባሕል ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ሽማግሌ፤ እና

ለ) የባሕል ፍርድ ቤቱ ሽማግሌዎች፡፡

፫/ የባሕል ፍርድ ቤት የፍርድ ቤቱ ፀሐፊና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ከ(፩-፫) የተገለፀው ቢኖርም የባሕል ፍርድ ቤቱ በአካባቢው ባሕል ሕግ እና እንደየ ባሕላዊ ፍርድ ቤቱ ልዩ ባሕሪ የተቋማቱን ዝርዝር አደረጃጀት እና አፈፃፀም በሚወጣው ደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡



2/ Recognition may be given to social institutions organized as customary courts that settle disputes based on customary laws. Particulars shall be determined by a regulation and directive to be issued.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-articles (1) and (2) of this Article, social institutions engaged in dispute resolution under customary laws are not prohibited by this proclamation to discharge their regular duties.

## 7. Structure of Customary Courts

1/ The Customary Courts being established from the nationalities customary courts, it shall have the following structure at Wereda or kebele level:

A) First Instance Customary Court, and

B) Appellate Court.

2/ Customary courts shall have the following organs:

A) Presiding Elder of the Customary Court, and

B) Elders of the Customary Court.

3/ Customary Court shall have Secretary of the the customary court and other staffs as necessary.

4/ Notwithstanding the provisions from Sub articles (1-3) of this Article, the institutional detailed structure and implementation of the customary court shall be determined by the regulation and directive to be issued accordance with the customary law of the locality and unique characteristics of the customary court.

## ፰. የባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን

፩/ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ተቀብሎ የማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡-

ሀ) የቤተሰብና እና ግለሰባዊ የፍትሐብሔር ጉዳይ፤

ለ) በግል አቤቱታ የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች እና የደንብ መተላለፍ ድርጊቶች፤

ሐ) በሌሎች ሕጎች ላይ በግልጽ ተለይተው የማየት እና የመወሰን ሥልጣን በተሰጣቸው ጉዳዮች፡፡

፪/ የባሕላዊ ፍርድ ቤት የሚቀርብለትን ጉዳይ ማየት የሚችለው ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በባሕላዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ፍቃዳቸውን በጽሑፍ ወይም በቃል ከሰጡ ብቻ ነው፡፡

፫/ በመደበኛ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች ተስማምተው በዚህ አንቀፅ በተመለከቱ ጉዳዮች ያላቸውን ጉዳይ ወደ ባሕላዊ ፍርድ ቤት እንዲመራላቸው ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(፩-፫) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባሕል ፍርድ ቤት የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማየት ከሚከተሉት መስፈርቶች መካከል ቢያንስ አንዱ መሟላት አለበት፡-

ሀ) ከተከራካሪ ወገኖች ቢያንስ የባሕል ፍርድ ቤት ሥልጣን ወሰን በሚገኝ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ ወይም ተወላጅ ከሆነ፤ ወይም

ለ) ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቋሚ ንብረት የባሕል ፍርድ ቤቱ የሥልጣን ወሰን በሆነው ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፤ ወይም

ሐ) የጉዳዩ መነሻ በባሕል ፍርድ ቤት የሥልጣን ወሰን ውስጥ የተጀመረ ወይም ፍፃሜ ያገኘ ከሆነ ነው፡፡



## 8. Customary Courts Judicial Power

1/ The Customary Court Shall have a jurisdiction ov the following matters:

A) Family and private civil matters;

B) Crimes cases submitted as private appeal a law transgression matters;

C) Other matters expressly authorized by oth laws.

2/ Customary Court shall have proceeding jurisdicti of a case only if the disputing parties give th consent either in writing or orally.

3/ Litigant parties in a regular court can request th cases mentioned in this Article to be referred to customary court based on mutual agreement.

4/ Without prejudice to the provisions from Sub-artic (1 – 3) of this Article, at least one of the followi criteria must be fulfilled in order for the Custom Court to proceed a case before it:

A) At least one of the disputing parties is a resid or was born in the local administrative u within the jurisdiction of the customary court

B) The immovable property subject to the disp is situated in the local administrative unit wit the jurisdiction of the customary court, or

C) The case leading to the dispute was initiated finalized within the jurisdiction of customary court.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ የተዘረዘሩት የአካባቢያዊ የዳኝነት ሥልጣን ማሳያዎች ጋር በተለየ መልኩ የሚያስቀምጥ የባሕል ሕግ በሚኖር ጊዜ የባሕል ሕጉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) ስር የተደነገገው ቢኖርም የባሕል ፍርድ ቤት በዓቃቤ ሕግ ክስ አቅራቢነት የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉትን ለመፈፀም ሥልጣን ይኖረዋል፡-

(ሀ) በክርክሩ ድርሻ ያላቸውን ወገኖች ማስታረቅ፤

(ለ) ክፍያ መወሰንና ማስፈፀም፤

(ሐ) የሚከፈል ካሳን መወሰን፤

(መ) ወጪና ኪሰራን ማስከፈል፡፡

፯/ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የቀረበለት ጉዳይ በባሕል ፍርድ ቤት እልባት ማግኘት አለበት ብሎ ካመነ ወይም የሚያዝ ሕግ ሲኖር በተከራካሪ ወገኖች ፍቃድ ጉዳዩን አይቶ መፍትሔ እንዲሰጥ ለባሕላዊ ፍርድ ቤት መምራት ይችላል፡፡

፰/ በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ በባሕል ፍርድ ቤት መታየት የጀመረን ጉዳይ ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ካልወሰነ በቀር ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለውም፡፡

፱/ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ባሕል ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚቀርበውን ቅሬታ ብቻ የማየት ሥልጣን አለው፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ ሽማግሌዎች

### ፱. የሽማግሌዎች የምርጫ መስፈርት

፩/ ሽማግሌ ሆኖ የሚመረጥ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሠራበትን አካባቢ የባሕል ሕግ እና እሴቶች የሚያውቅና የሚያከብር፤



5/ When there is a local customary law that determines jurisdiction in a different way than what is provided under Sub-article (4) of this Article, such customary law shall prevail.

6/ Notwithstanding with the provision of Sub-article 1(B) of this Article, the Customary Court shall have the following executive powers in relation to criminal matters instituted by the Public Prosecutor:

A) Reconciling the parties under dispute;

B) Determining amount of payment and execution of such order;

C) Determining compensation to be paid;

D) Determining on litigation related costs.

7/ When a court of jurisdiction seizing the matter believes that the case should be resolved by the Customary Court, or there is a law requiring so, it may refer the case to the Customary Court for its resolution based on the consent of the parties.

8/ A court shall not have the power to entertain a matter pending before a customary court with the consent of the parties except in accordance with Article 34 sub-article 2 of this Proclamation.

9/ The Customary Court shall have the jurisdiction only over appeals against the final decisions of the First Instance Customary Court.

## PART FOUR
## ELDERS

### 9. Criterion for Elders Election

1/ A person must fulfill the following criteria to be elected as an elder of a Customary Court:

A) person who knows and respects the customary law and social values of the place where the Customary Court operates;

ለ) በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ ዕርቅ የማውረድ ብቃትና ልምድ ያለው፤

ሐ) ሽማግሌ ሆኖ ለማገልገል ፍቃደኛ የሆነ፤

መ) በመደለያ ወይም እጅ መንሻ ሲደለል እንደማይችል በማኅበረሰቡ የሚታመን ሰው፤

ሠ) የአዕምሮ ጤና እክል ወይም ግዴታውን ለመወጣት የማያስችል የአካል ጉድለት ወይም የጤና ችግር የሌለበት፤

ረ) የወንጀል የጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለው ወይም ጥፋተኛ ተብሎ ከሆነ የተሰየመ::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ሽማሌዎች ማሟላት ያለባቸው ተጨማሪ መስፈርቶች በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ ሊወሰን ይችላል::

## ፲. የሽማግሌዎች ብዛት

የሽማድሌዎች ቁጥር በክልሉ ባሉ የተለያዩ ብሔረሰቦች ላይ የተለያየ ሥርዓት በመኖሩ ፍትሐዊነትን እና ተዓማኝነት የሚፈጥር የሽማግሌ ቁጥር የሚይዝ ሆኖ ዝርዝር ብዛቱ እንደየ ባሕላዊ ፍርድ ቤቱ ልዩ ባሕሪ በደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል::

## ፲፩. የምርጫ ሂደት

፩/ የወረዳ ፍርድ ቤት የሽማግሌዎችን ምርጫ የሚያስተባብርና የሚመራ ኮሚቴ ያቋቁማል::

፪/ ኮሚቴው ሽማግሌዎችን ለማስመረጥ የቀበሌው አስተዳዳሪ ነዋሪዎችን ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል::

፫/ የሽማግሌዎች ሹመት እና ከሹመት መነሣት በባሕላዊ ሥርዓቱ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፤ ዝርዝር ሥርዓቱ በደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል::



B) A person who has acceptance and with enou experience and qualities on reconciliation amo the community;

C) Willing to serve as an elder;

D) A person trusted by the community for integrity from kickback and palm greasing;

E) A person who does not have mental or phys impairment or incapable from performing duties;

F) He is not convicted of crime; or he is reinst in case he had been previously convicted of s

2/ Without prejudice to Sub-article (1) of this Art additional criteria for election of elders may determined by a regulation or directive to be issu

## 10. Number of Elders

Given the variations in the customary practice different nationalities in the region, the number of e in the Customary Courts shall be determined in a m that ensures equity and trust, taking into account sp contexts. Particulars shall be determined by a regu and directive to be issued.

## 11. Election Procedures

1) A Wereda court shall establish a committe coordinates and leads the election of elders.

2) The committee shall request the kebele admini to convene the meeting of the Kebele reside select elders.

3) The appointment and removal of elders sh determined in accordance with the customary Detail procedures shall be determined by a reg and directive to be issued.

## ፲፪. የሽማግሌዎች ቃለ መሐላ

ለባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆነው የተመረጡ ሽማግሌዎች የምርጫ ውጤት ከታወቀ በኋላ የአካባቢው ባሕል ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ቃለ መሐላ እንዲፈጽሙ ይደረጋል፡፡

## ፲፫. የሽማግሌዎች የሥራ ዘመን

፩/ የሽማግሌዎች የሥራ ዘመን እንደየ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶቹ የባሕል ሕግ የሚወሰን ሲሆን ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚወሰነው የሥራ ዘመን ቢኖርም ሽማግሌው የብቃት ወይም የሥነምግባር ጉድለት ያለው እንደሆነ ጥቆማ ወይም ቅሬታ ሊቀርብበት ይችላል፡፡ የሚቀርበውንም ቅሬታ የአካባቢውን ነዋሪ ስብሰባ በመጥራት አጣርቶ ከተረጋገጠበት በየትኛውም ጊዜ ከኃላፊነቱ ማንሣት ይቻላል፡፡

## ፲፬. ከሥነምግባር እና ብቃት ማጣት ምክንያት ውጭ ሽማግሌ ከሥራ የሚነሣበት አግባብ

አንድ ሽማግሌ በሚከተሉት ምክንያቶች ከሥራው ሊነሣ ይችላል፡-

፩/በፍላጎቱ፤

፪/ በሞት፣ በአካል ጉዳት ወይም ሥራውን መቀጠል በማያስችሉ ሌሎች የጤና እክሎች፤

፫/ መኖሪያ አድራሻን በመቀየሩ ምክንያት ሥራውን መቀጠል ካልቻለ፤

፬/ የይግባኝ ሰሚ ባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌ ሆኖ ከተመረጠ፤

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተዘረዘሩት ሽመግሌዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያላሟላ ከሆነ ወይም አድልኦ ከተገኘ፡፡



## 12. Oath of the Elders

Upon announcement of the results, the elected elders fo the Customary Court shall take an oath in accordanc with the customary law of the area where the Customar Court operates.

## 13. Terms of Service of Elders

1/ The terms of service of elders shall be determined accordance with the customary law of the localit Particulars shall be determined by a directive.

2/ Notwithstanding what to be determined under Su article (1) of this Article, capacity or integr limitations of an elder may be challenged throu whistleblowing or complaint handling procedures. the complaint is substantiated by a meeting of t Kebele residents, the elder may be removed at a time.

## 14. Removal of Elders Other than La of Capacity and Ethics

An elder may be removed from his duty based on following grounds:

1) Up on his own will;
2) By death, physical injury or health issue leading inability to continue to discharge his duty;
3) Inability to continue discharging his duty by rea of change of his residence;
4) If he is elected as an Appellate Customary C Elder;
5) If he failed to fulfill at least one of the listed crit under Article 9 Sub-article (1) of this Proclama that elders should meet or if discrimination is t found.

## ፲፭. ሥራ መልቀቅን ማሳወቅ እና የማሟያ ምርጫ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፩-፫) መሠረት ሥራውን መልቀቅ ከፈለገ አንድ ወር አስቀድሞ ለኮሚቴው ማሳወቅ አለበት።

፪/ የባሕል ፍርድ ቤት ሽማግሌን ለማስመረጥ በተቋቋመው ኮሚቴ መሠረት በጎደለው ሽማግሌ ቦታ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተገለፀውን ሥነ-ሥርዓት በመከተል ምትክ ሽማግሌ እንዲመረጥ ያደርጋል።

## ፲፮. የሥራ ነጻነት

፩/ የባሕል ፍርድ ቤቶች ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከግል አመለካከት እና ከማንኛውም አካል ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በባሕል ሕግና በክልሉ እሴቶች ላይ ብቻ ተመሥርተው በፍትሕ እና በፍትሕ ሥራቸውን ይመራሉ።

፪/ ሽማግሌዎች በህሊናቸው፣ በባሕል ሕግና በማኅበረሰቡ እሴቶች ብቻ የሚመሩ ይሆናል።

፫/ ሽማግሌዎች ሥልጣናቸው በሆነ ጉዳይ ላይ ወይም በቅን ልቦና ሥልጣን እንዳላቸው አስበው በባሕል ሕግ መሠረት በሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ ምክንያት የወንጀል እና የፍትሐብሔር ተጠያቂነት የለባቸውም።

፬/ ሽማግሌ የሥነ ምግባር ጉድለት ወይም የብቃት ማነስ ያለበት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የሥራ ዘመኑን ሳይጨርስ ከሥራው አይነሣም።

## ፲፯. የሽማግሌ ግዴታ

ማንኛውም ሽማግሌ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

፩/ ሥራው የሚፈልገውን ሥነምግባር ማክበር፤

፪/ ፆታን፣ ሃይማኖትን፣ ጎሳን፣ ዕድሜን፣ የኢኮኖሚ ሁኔታን፣ የፖለቲካ አመለካከትንና ማንኛውንም ሁኔታ መሠረት በማድረግ አድልኦ ከመፈፀም መቆጠብ፤



## 15. Notification of Resignation and Replacement Election

1/ If an elder of the Customary Court wants to resign in accordance with Article 14, Sub-articles (1-3) of this Proclamation, he shall give one month prior notice to the committee.

2/ The vacant elder shall be elected following procedures of Article 11 of this proclamation through the established committee to cause the election of customary court elder.

## 16. Independence of Service

1/ Customary Courts shall exercise their function based on customary law and values of the region guided only by sense of justice being free from pressures of politics, religion, personal outlook and any organ.

2/ Elders shall be guided by their own conscience, customary law and values of the society.

3/ Elders shall not be subjected to civil and criminal liability for their decisions and orders they render, pursuant to the customary law, on matters falling under their power or matters which they deem, in good faith, fall within their power.

4/ Elders shall not be removed from their duty before the lapse of their term of office unless proven to have shown capacity or ethical limitations.

## 17. Obligations of Elders

Any elder shall have the following obligations:

1/ Respecting the required code of conduct;

2/ Refraining from discrimination based on gender, religion, ethnicity, age, economic status, political attitude and any other ground;

፫/ በጥቅም ከመሥራት ነፃ መሆን፤

፬/ ምሳሌ መሆን የሚችል፣ መልካም ፀባይ እና የባሕል ፍርድ ቤቱን መልካም ስም መገንባት የሚችል የግል ሕይወት ያለው፤

፭/ ሚስጢር መጠበቅ፤

፮/ የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆን፤

፯/ የባሕላዊ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ማንኛውንም ውሳኔ የራሱ አድርጎ መውሰድ፤

፰/ የግል ጥቅሙ ያለበት ጉዳይ ከቀረበ ከጉዳዩ እራሱን ማንሳት፡፡

## ፲፰. የሰብሳቢ ሽማግሌ ሥራ እና ኃላፊነት

ሰብሳቢ ሽማግሌ በተጨማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ሽምግልና የሚታይበትን ቀን በመወሰን ሽማግሌዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ማሳወቅ፣

፪/ የባሕል ፍርድ ቤቱን የሥራ ክንውን ሪፖርት ለሚመለከተው አካል መላክ፤

፫/ ተከራካሪዎችንና ምስክሮችን ቃለ መሐላ ማስፈፀም ወይም እንዲፈፅሙ ማድረግ፡፡

## ፲፱. የባሕል ፍርድ ቤት ፀሐፊ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት አንድ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

፪/ የባሕል ፍርድ ቤት ፀሐፊ ሆኖ የሚመደብ ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ስር የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

፫/ የባሕል ፍርድ ቤት ፀሐፊን አወዳድሮ የሚመድበው የወረዳው ፍርድ ቤት ሽማግሌዎቹ ወይም የባሕል ሕጉ በሚያስቀምጠው ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡



3/ Being free from working for personal gain;

4/ Possession of exemplary behavior and a personal lif that builds the good will of the Customary Court;

5/ Keeping confidentiality;

6/ Refraining from becoming member of any politica party;

7/ Taking all decisions of the Customary Court as tha of his own;

8/ Withdrawal of himself from the case if same havin conflict of interest is submitted.

## 18. Duty and Responsibility of Presidin Elder

Presiding Elder shall have the following additiona obligations:

1/ Fixing a day for hearing and notifying other elder and concerned organs;

2/ Submitting report of Customary Court to th concerned organ;

3/ Making disputants or witnesses take oath or ensurin same.

## 19. Secretary of Customary Court

1/ A Customary Court shall have one secretary.

2/ A person to be assigned as secretary of Customar Court shall fulfill the criteria specified under Artic 9, Sub-articles (1) (B), (C) and (D) of th proclamation.

3/ The Wereda Court shall assign secretary c Customary Court on competition based on procedure to be issued by the elders or customar law.

4/ Detail implementations of this Article shall b determined by a regulation and directive to b issued.

## ፳. የፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

፩/ ፀሐፊው የሚከተሉትን ተግራት ያከናውናል፡-

ሀ) በሽምግልና ላይ በመገኘት በቃል የሚሰጡ አቤቱታና መልስ፣ የቃል ክርክር፣ የምስክሮች ቃል፣ የሚሰጡ ውሳኔዎች እና ትዕዛዞችን መፃፍ፤

ለ) ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ፊርማቸውን ማስፈረም፤

ሐ) ክስ የሚሰማበት የመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ በመያዝ ለከሳሽ ማሳወቅ፤

መ) የሚቀርቡትን ማስረጃዎች መቀበልና በሥርዓት መያዝ፣ መዝገብ ማደራጀት እና ቁጥር መስጠት፤

ሠ) የውሳኔ ግልባጭ መስጠት፤

ረ) የሥራ ክንውን ሪፖርትን ማደራጀት፡፡

፪/ ፀሐፊው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) ስር ስለ ሽማግሌዎች የተዘረዘሩ ግዴታዎች፤

ለ) ባለመግባባት ውስጥ ላሉ ግራ ቀኝ ወገኖች ክስ፣ አቤቱታና መልስ አለማዘጋጀት፤

ሐ) በሽማግሌዎች የሚሰጠውን ማንኛውንም የባሕላዊ ፍርድ ቤት ሥራ ማከናወን፡፡

## ፳፩. ተጠያቂነት

ሽማግሌዎችና ፀሐፊ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱት ግዴታዎችና በሌሎች ሕጎች ያላቸውን ኃላፊነቶችን ሳይወጡ ከቀሩ፣ በባሕል ሕግ መሠረት ወይም በሚወጣ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የሚጠየቁ ይሆናል፡፡

## ፳፪. ጥቅማጥቅም

የባሕል ፍርድ ቤት ፀሐፊን የሚመለከቱ ጥቅማጥቅሞች እና ክፍያዎች እንደ አስፈላጊነቱ በሚወጣ ደንብ እና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡



## 20. Duty and ResponsibilitySecretary

1/ The Secretary shall perfom the following functions:

A) Presenting at the hearing and accurately recording oral applications, defenses, oral litigation, witness testimonies, judgments and orders to be rendered.

B) Making the elders sign on orders and judgments rendered;

C) Fixing date for the first hearing and notifying same to the plaintiff;

D) Receiving and properly handling submitted evidence, organizing files and numbering;

E) Giving copy of a judgement;

F) Organizing a report.

2/ The Secretary shall have the following obligations:

A) Those duties enumerated under Article 17 (1-5) of this Proclamation about the elders;

B) Refraining from preparing statements of claims and defenses for parties under disputanting;

C) Performing any task of the customary court assigned to him by the elders.

## 21. Accountability

Elders and secretary who fail to discharge duties entrusted to them in accordance with this proclamation or other relevant laws shall be accountable in accordance with the customary law or a regulation to be issued and other relevant laws.

## 22. Benefits

Benefits and other payments concerning secretary Customary Court Secretary shall be determined by a regulation or directive to be issued as necessary.

# ክፍል አምስት

# የባሕል ፍርድ ቤት ማስቻያ ስፍራ፣ ጉዳይ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ

## ፳፫. የባሕል ፍርድ ቤት ማስቻያ ቦታ እና ጊዜ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ቦታ ላይ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተከራካሪ ወገኖችን የግል ሕይወት፣ የሕዝብ ሞራልና ደኅንነትን ለመጠበቅ ወይም የባሕል ሕጉ ለሚፈቅደው ሌላ ምክንያት ጉዳዩ ለብቻ እንዲሰማ ማድረግ ይችላል፡፡

፫/ የባሕል ፍርድ ቤት ሽምግልና የሚያከሄድበት ቦታ እንደ ጉዳዩ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ከሚከተሉት በአንዱ ሊሆን ይችላል፡-

(ሀ) በዛፍ ጥላ ስር፤

(ለ) በውኃ ዳር፤

(ሐ) ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀ ወይም በተሰጠ አዳራሽ ውስጥ፤

(መ) የባሕል ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት የተመረጡ ሌሎች ቦታዎች፡፡

፬/ የባሕል ፍርድ ቤቱ በሚቀርበው ጉዳይ ብዛት መሠረት ወይም የባሕል ሕጉን መሠረት በማድረግ በቋሚነት ሽምግልና የሚያከሄድበትን ጊዜ መወሰን አለበት፡፡

፭/ የባሕል ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት ወይም በአካባቢው የባሕል ሕግ መሠረት ጉዳዮችን ለማየት የሚወስንበትን ጊዜ ለማኅበረሰቡ ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፬) ስር የተደነገገው ቢኖርም ሰብሳቢ ሽማግሌ ያደረን ወይም አስቸኳይ ጉዳይን ለማየት ሽምግልና የሚኖርበትን ተጨማሪ ቀን ሊወስን ይችላል፡፡ ይህንንም ለሽማግሌዎች እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ማሳወቅ አለበት፡፡



# PART FIVE

# HEARING PLACE, PROCEDURES OF APPLICATION AND DECISION-MAKING PROCESS OF CUSTOMARY COURTS

## 23. Hearing Place and Time of Customary Courts

1/ Customary Court shall conduct its trial at a place open to the public.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-article (1) of this Article, it can hear the case in camera where it is required to protect privacy of the disputing parties, morality and security of the public or another ground as may be provided under customary laws.

3/ The place of conducting trial (hearing) being decided based on circumstance of the case; it may be one of the following:

A) Under shade of a tree;

B) Near water peripheries;

C) In a hall prepared or given for this purpose;

D) In other places as allowed by the customary law.

4/ The customary court shall determine the permanent time of hearing based on the number of cases or based on the customary law.

5/ The Customary Court shall announce the date of hearing to the community pursuant to Sub-article (4) of this Article or the local customary law.

6/ Notwithstanding to Sub-article (4) of this Article, presiding elder may fix additional day for hearing in order to entertain ongoing or urgent cases. He must notify same to the elders and concerned bodies.

### ፳፬. ፈቃደኝነት የሚረጋገጥበት ሁኔታ

፩/ ለባሕል ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ ያቀረበ ሰው በባሕል ፍርድ ቤት ለመስተናገድ ፈቃዱን እንደሰጠ ይቆጠራል፡፡

፪/ ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ከቀረበ በኋላ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ከመደረጉ በፊት ጉዳዩ በባሕል ፍርድ ቤት እንዲታይ ፈቃደኛ መሆኑ ተጠይቆ ይህንኑ ፈቃደኝነቱን በጽሑፍ ወይም በቃል በመግለጽ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ጉዳዩ በባሕላዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ማንሣት አይችልም፡፡

### ፳፭. ሥራ ላይ የሚውል ሕግ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት ሥራ ላይ የሚያውለው ሕግ የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሠራበት አካባቢ ያለ የባሕል ሕግ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው ቢኖርም የባሕል ሕጉ ከሚከተሉት ጉድለቶች ውስጥ አንዱን ቢኖረው ተፈፃሚነት አይኖረውም፡-

ሀ) የተፈጥሮ ፍትሕን የሚቃረን ከሆነ፤ ወይም

ለ) ርትዕን የሚቃረን ከሆነ፤ ወይም

ሐ) የማኅበረሰቡን ሞራልና ግብረ-ገብ የማያከብር ከሆነ፤ ወይም

መ) በሰዎች መካከል በእምነት፣ በጾታ፣ በመልክ፣ በእድሜ፣ በአካል ጉዳት፣ በብሔር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በሀብት ወይም በሌላ ምክንያት አድልኦን የሚፈጥር ከሆነ፤ ወይም

ሠ) ሰብዓዊ መብትን የሚፃረር ከሆነ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ስር የተደነገገው ቢኖርም የባሕል ፍርድ ቤቶች ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የኅበረተሰብ ክፍሎችን የሚያበረታቱ የባሕል ሕጎችንና አሠራሮችን ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡



### 24. Conditions of Proofing of Consent

1/ A person who filed his suit or application to Customary Court shall be presumed to have giv his consent to be adjudicated by customary court

2/ The defendant who appeared after the summon duly served upon him shall be asked his consen verify whether he desires his case to be adjudica by Customary Court before submitting his statem of defense and he shall confirm such either writing or orally.

3/ A plaintiff or defendant who gave his consent to jurisdiction of Customary Court can not revoke

### 25. Applicable Laws

1/ The law which the Customary Court ought to ap shall be the customary law of the place wher carries out its function.

2/ Notwithstanding with the provision of Sub-article of this Article, the customary law shall not applicable if it has one of the following short comi

A) Where it contravenes with natural justice; o

B) Where it does not respect equity; or

C) Where it contradicts with ethics and morali the community; or

D) Where it discriminates between people base religion, sex, appearance, age, disab nationality, political attitude, wealth or other grounds; or

E) Where it violates human rights.

3/ Without prejudice to the provision of Sub-articl of this Article, Customary Courts may customary laws and practices which may favo rights of women, children, people with disa and other vulnerable segments of the society.

## ፳፮. የጉዳይ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

፩/ ጉዳዩ በባሕል ፍርድ ቤት እንዲታይለት የሚፈልግ ሰው የባሕል ፍርድ ቤቱን ፀሐፊ በማናገር ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ ያስይዛል፡፡

፪/ የባሕል ፍርድ ቤቱ ጉዳይን መስማት ከመጀመሩ በፊት በባሕል ሕጉ መሠረት መገኘት ያለባቸው ሽማግሌዎች መሟላት አለባቸው፡፡

፫/ ጉዳዩ ለመሰማት በተቀጠረበት ቀን ከሳሹ የባሕል ፍርድ ቤቱ ጋር ቀርቦ ጉዳዩን ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ የባሕል ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ክስ ወይም አቤቱታ ለማየት ሥልጣን የሌለው ከሆነ ወይም ከሳሽ በባሕል ሕጉ መሠረት ከጉዳዩ ጥቅም የሌለው ከሆነ ወይም የክስ ምክንያት የለውም ብሎ ያመነ እንደ ሆነ ተከሳሽን መጥራት ሳያስፈልግ ጉዳዩን ዘግቶ አቤቱታ አቅራቢን ወይም ከሳሽን ማሰናበት ይችላል፡፡

፭/ ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ሰው በባሕል ፍርድ ቤት ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ ሽማግሌዎች ባመኑበት ሰው አማካኝነት መጥሪያ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት መጥሪያ ደርሶት የቀረ ሰው ለሁለተኛ ጊዜ ጥሪ ይደረግለታል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ስር በተደነገገው መሠረት ጥሪ የተደረገለት ሰው መቅረብ ካልቻለ በአከባቢው የባሕል ሕግ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

፰/ ተከሳሽ በጥሪው መሠረት በቀነ ቀጠሮ ከቀረበ የቀረበበት ክስ ወይም አቤቱታ በባሕል ፍርድ ቤቱ ፊት ሊገለፅለት ይገባል፡፡

## 26. Application Procedures of a Case

1/ A person who desires his case to be adjudicated by Customary Court shall contact Secretary of the Customary Court to fix date of the hearing.

2/ The required number of elders of the Customary Court need to be fulfilled in accordance with customary law before commencement of hearing of the case.

3/ The plaintiff shall appear and present his case to the Customary Court on the date of appointment.

4/ The Customary Court shall dismiss the case and farewell the plaintiff without the need to call the defendant where the suit or application brought does not fall under its jurisdiction or the plaintiff has no benefit from the suit in accordance with customary law or where it believes that there is no cause of action.

5/ Summon shall be sent to a person against whom the suit or application is instituted through a person trusted by elders of the Customary Court to appear with his statement of defense.

6/ Where a person failed to appear after summon was duly served upon him in accordance with Sub-article (5) of this Article, he shall be served for a second time.

7/ Necessary measure shall be taken in accordance with local customary law against a person who failed to appear after duly summoned according to Sub-article (6) of this Article.

8/ The suit or application shall be explained at the hearing to the defendant if he appeared after duly served with the summons.

፱/ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ ከሰማ በኋላ በባሕላዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት ፍቃደኝነቱ ከተረጋገጠ የባሕል ፍርድ ቤቱ የቀረበበት ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ ማዘዝ ወይም ሌላ እርምጃ መውሰድ ይችላል።

፲/ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ ያመነ እንደ ሆነ የባሕል ፍርድ ቤቱ በሚሠራበት አከባቢ ባለው የባሕል ሕግ መሠረት ውሳኔ ወይም አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።

፲፩/ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደ ሆነ የባሕል ፈርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ መንገድ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት ይችላል።

፲፪/ ባለመግባባት ውስጥ ያሉ ወገኖች የጉዳዩ መሰማት ሂደት ተጀምሮ ከቀጠለ በኋላ ሳይቀርቡ የቀሩ እነደሆነ የባሕል ፍርድ ቤቱ በባሕል ሕጉ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል።

፲፫/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩-፲፪) የተደነገገው ቢኖርም የባሕል ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ሲመለከት የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሠራበት አከባቢ ያለውን የባሕል ሥነ ሥርዓት ሕግን መከተል ይችላል።

፲፬/ ከሳሽ የሚያቀርበው ማንኛውም ክስ ወይም አቤቱታ ወይም ተከሳሽ የሚያቀርበው ማንኛውም መልስ በጽሑፍ ወይም በቃል ሊሆን ይችላል።

፲፭/ በባሕል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳይ ላይ ማንኛውም ወገን በሕግ ጠበቃ ክርክር ማቅረብ አይችልም።

፲፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪ ወገኖች በቤተሰብ አባል ወይም የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሠራበት አከባቢ ባለው የባሕል ሕግ መሠረት ለሚፈቀድለት ሰው መወከል ይችላሉ።



9/ If the defendant confirms his consent to be adjudicated by the customary court after he hears the statement of claim, the Customary Court may order to defend or take another measure.

10/ Where the defendant admits the suit or application against him, the Customary Court may give judgement or necessary order in accordance with the customary law of the place where the Customary Court carries out its function.

11/ Where the defendant denies the suit against him, the Customary Court may give decision after ascertaining the matter in appropriate manner.

12/ Where the disputing parties failed to appear after hearing of the case has commenced, the Customary Court may take an appropriate measure in accordance with customary law.

13/ Notwithstanding to provisions of Sub-article (1-12) of this Article, the Customary Court may follow any other procedure of customary law of the place where it carries out its functions.

14/ Any suit or application instituted by a plaintiff or the defense presented by a defendant may be in writing or orally.

15/ No party can be represented by legal attorney on any case proceeding before the Customary Court.

16/ Without prejudice to the provision of Sub-article (15) of this Article, parties may be represented by member of the family or by another person who is allowed by the customary law of the place where the Court carries out its function.

## ፳፯. ምስክር መስማት

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት የያዘውን ጉዳይ ያብራራል ብሎ ያመነን ወይም በተከራካሪ ወገኖች የተጠቀመን ማንኛውንም ሰው እንዲቀርብ ጥሪ ያደርግለታል፡፡

፪/ ምስክር እንዲሆን በባሕል ፍርድ ቤት ጥሪ የደረሰው ሰው በቂ ባልሆነ ምክንያት ለመቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ የባሕል ፍርድ ቤቱ በባሕል ሕግ መሠረት እንዲቀርብ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ወይም በቀበሌ አስተዳደር በኩል ቁጥጥር ስር ውሎ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡

## ፳፰. መሐላ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት ክስ፣ አቤቱታ፣ መልስ እንዲሁም ምስክር ከመስማቱ በፊት ተከራካሪ ወገኖች ወይም ምስክሮች የባሕል ፍርድ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ባሕል መሠረት ወይም በግለሰቡ እምነት መሠረት መሐላ እንዲፈፅም ያደርጋል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ከሌላ ሰው ተለይቶ በአቤቱታ ውስጥ የተገለፀን ድርጊት መፈጸሙን ወይም አለመፈፀሙን መሐላ ፈፅሞ እንዲታመንለት ለባሕል ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ የባሕል ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርቡ ካደረገ በኋላ በአከባቢው ባሕል መሠረት መሐላ ፈፅመው እንዲታመኑ ያደርጋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ማመልከቻ ቀርቦበት መሐላ ፈጽሞ ለመታመን ፍላጎት የሌለው ሰው የተጠረጠረበትን ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮ የባሕል ፍርድ ቤቱ አስፈላጊውን የውሳኔ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡



## 27. Witness Hearing

1/ A Customary Court shall summon any witness the customary court deemed so or mentioned by the parties to testify about the case at hand.

2/ Where it is understood that a person called to testify failed to show interest to appear without good cause, the Customary Court shall take necessary measure to compel the attendance of such person in accordance with the customary law or issue arrest warrant so that Kebele administrator shall secure his attendance.

## 28. Oath

1/ Before hearing a suit, defense or witness, the Customary Court shall make the parties and witnesses take oath in accordance with the custom of the place where the Customary Court is located or based on religion of the individual.

2/ Any person may apply to the Customary Court by taking oath to be trusted whether he committed or omitted the act he is suspected of as specified in the application.

3/ Where the application is lodged in accordance with Sub-article (2) of this Article, the Customary Court shall call concerned bodies and make them take oath based on custom of the locality to be trusted.

4/ Where a person failed to give his consent to take oath to be trusted in accordance with Sub-articles (2) and (3) of this Article, he shall be presumed to have committed the act and the Customary Court shall take necessary measure against him based on the customary law.

## ፳፱. በአካል ተገኝቶ ጉዳዩችን ማየት

ሽማግሌዎች የመሬት ድንበር አለመግባባት፣ በመንገድ የመጠቀም መብት የማግኘት፣ ከወንዝ ውኃ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ እና አስፈላጊ ሆኖ የተገኙ ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ለግጭቱ ምክንያት የሆነ ቦታ ላይ ተገኝቶ ማጣራት ይችላሉ፡፡

## ፴. የውሰኔ አሰጣጥ ሂደት

፩/ የባሕል ፍርድ ቤቱ የቀረበለት ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖች እርቀ ስምምነት እንዲያልቅ ጥረት ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጉዳዩ በእርቀ ስምምነት ከተጠናቀቀ የባሕል ፍርድ ቤቱ (ችሎቱ) የስምምነቱን ይዘት መዝግቦ ተከራካሪዎችን ያሰናብታል፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የዕርቀ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ስምምነቱ በባሕል ፍርድ ቤቱ እንደተሰጠ ውሳኔ ተቆጥሮ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(፩-፫) መሠረት ጉዳዩ በተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረግ የዕርቀ ስምምነት መፍትሔ መስጠት ካልተቻለ ሽማግሌዎች ጉዳዩን በማጣራት የአከባቢው የባሕል ሕግ የሚፈቅደውን አካሄድ በመከተል የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጣሉ፡፡

፭/ ሽማግሌዎች ለሰጡት የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መነሻ ያደረጉትን የባሕል ሕግ እና ምክንያት በግልፅ ለተከራካሪ ወገኖች በባሕል ፍርድ ቤቱ (ችሎቱ) ላይ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

፮/ ሽማግሌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) መሠረት በሰጡት የዕርቅ ውሳኔ ላይ ተከራካሪ ወገኖች እንዲስማሙ እና የተስማሙበትን እንዲፈፅሙ ለማስማማት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ተከራካሪ ወገኖችን ማስማማት ካልተቻለ ቅሬታውን ማቅረብ ለሚፈልግ ወገን የይግባኝ መብት ይጠበቃል፡፡



## 29. In Person Observation

Elders of the Customary Court may physically pres a place to observe and ascertain disputes as deem necessary relating to boundary of land, right of wa of river water and other cases.

## 30. Decision Making Process

1/ The Customary Court shall exert efforts to re disputes through mediated agreement betwee disputing parties.

2/ Where the case is completed in mediated agree accordance with Sub-article (1) of this Article Customary Court shall record content of agreement and dismiss the parties.

3/ If mediated agreement is reached in accordance Sub-article 2 of this Article, it shall be considere the decision given by Customary Court and wi executed accordingly.

4/ Where the case is not settled by mediated agreem reached between the disputing parties in accorda with Sub-articles (1-3) of this Article, elders of Customary Court shall give a mediated judgemen order in accordance with the customary law.

5/ The elders shall explain for the parties about the customary law and the reason on which they relie reach mediated judgement or order.

6/ Elders should endeavor to enable the disput parties to reach agreement on the decisions given accordance with Sub-article (4) and (5) of t Article and implement the same.

7/ If it is impossible to make disputing parties rea agreement in accordance with Sub-article (6) this Article, the aggrieved party has the right appeal.

## ፴፩. የእርቅ ውሳኔ ዓይነት

፩/ የባሕል ፍርድ ቤቱ ከሚከተሉት የውሳኔ ዓይነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ አጣምሮ መስጠት ይችላል፡-

ሀ) ጥፋተኛ መሆኑን ያረጋገጠን ሰው መምከር እና ማስጠንቀቅ፤

ለ) ካሳ፣ ንብረት ማስመለስ፣ ዋጋ መወሰን፣ ወይም የንብረትን ግምት ማስከፈል፣ ከኢኮኖሚ ጉዳት ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ የትኛውንም ጥያቄ ማስከበር፤

ሐ) የባሕል ሕግ እና ሥርዓትን መሠረት በማድረግ የአገልግሎት ክፍያ መወሰንና ማስፈጸም፤

መ) የተከሰሰ ወገን አንድን ድርጊት ተመልሶ እንዳይፈፅም ወይም እንዲፈፅም ማድረግ፤

ሠ) ወጪ እና ኪሳራ፤

ረ) የጉልበት ሥራ፤

ሰ) የገንዘብ ቅጣት፤

ሸ) የባሕል ፍርድ ቤቱ በሚሠራበት አካባቢ ባሉ የባሕል ሕጎች ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች ውሳኔዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባሕል ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የውሳኔ ዓይነቶች ሲሰጥ በአካባቢው የባሕል ሕግ መሠረት በገንዘብ ወይም በዓይነት እንዲፈፀም ሊወሰወን ይችላል፡፡

## ፴፪. ክስን ስለመተው

፩/ ከሳሽ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በእርቅ ምክንያት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ክሱን ሊያነሣ ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ የተነሣ ክስ እንደገና ሊታይ አይችልም፡፡

## 31. Types of Decision

1/ The Customary Court may give one or combining more of the following judgements:

A) Advising and giving admonition to the person a fault;

B) Compensation, returning property, deciding th value or amount of the property, or causin payment of property value, upholding an request concerning damage to economic rights;

C) Order and execute service payments based o Customary law and procedures;

D) Making the sued person do or refrain from doin a specific act;

E) Costs and damages;

F) Compulsory labor;

G) Fine;

H) Oher kinds of measures as acceptable by th customary law of the local area where th customary court operates.

2/ Without prejudice to the provision of Sub- article ( of this Article, the Customary Court may mal orders under mentioned above to be executed in ca or in kind.

## 32. Withdrawal of Claim

1/ A plaintiff may withdraw his claim, before decision rendered by the customary court, due to reconciliati or for any other reasons. A withdrawn claim cann be instituted again.

፬/ የባሕል ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በክስ ማንሣት ወቅት ከሳሽ በክሱ ምክንያት በተከሳሽ ላይ የደረሰ ኪሳራና ወጪ ካለ ከሳሽ እንዲሸፍን ሊያዝ ይችላል፡፡

## ፴፫. ይግባኝ

፩/ የባሕላዊ ይግባኝ ሥርዓት ያለው የባሕል ፍርድ ቤት በሆነ ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ የባሕል ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ለይግባኝ ሰሚ የባሕል ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በባሕላዊ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታው ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከሆነ ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡-

ሀ) የተከራካሪ ወገኖችን የእኩልነት መብት የማያከብር የባሕል ሕግ ሥራ ላይ ማዋል፤

ለ) የመሰማት መብት ወይም የቀረበውን ክርክር ለማረጋገጥ በአንድ ወገን የቀረበ ወሳኝ የሆነ ማስረጃን አለመቀበል፤

ሐ) በሕገ መንግሥት እና አገራችን በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶች ውስጥ የተገለፁ ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶችን የሚጥስ የባሕል ሕጎች እና አሠራሮችን ሥራ ላይ ማዋል፡፡

መ) ከሥልጣኑ ውጭ የሆነ ጉዳይ አይቶ የወሰነ እንደሆነ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ በፍሬ-ነገር ደረጃ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፬/ የባሕል ፍርድ ቤት በሚሰጠው የእርቅ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው ከተሰጠ ቀን ጀምሮ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ መጠየቅ አለበት፡፡



4/ The customary court may order the compensate the costs incurred by the there was cost and damge due to the cla

## 33. Appeal

1/ In case the customary law has an appeal person who is aggrieved by decision Instance Customary Court may take his a Appeallate Customary Court.

2/ A person who is aggrieved by final dec Customary Court may take his appeal Court if his grievance is related to following:

A) Applying customary law which unde right to equality of disputing parties;

B) Overlooking the rights to be heard o evidence presented by a disputing pa

C) Applying customary law or pract violates human rights and basic recognized under the Constitut international human rights instrumen by our country.

D) If it heard and decided out of its jurisd

3/ The decision rendered by wereda cour instance court pursuant to Sub-article (2 Article shall be final on question of facts.

4/ A person who has grievance on decision or Customary Court shall request copy of the within 15 days from the date of the decision.

፭/ የባሕል ፍርድ ቤቱ የውሳኔው ግልባጭ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ግልባጭ ለጠየቀው ወገን መስጠት አለበት፡፡

፮/ በባሕል ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለበት ሰው ግልባጩን ከወሰደ ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(፬ እስከ ፮) ስር የተደነገገው ቢኖርም የይግባኝ ባሕላዊ ፍርድ ቤት ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት አሳማኝ ምክንያት መቅረቡን ከተረጋገጠ ከላይ በተጠቀሰው ቀነ ገደብ ሳይገደብ የውሳኔ ግልባጭ መስጠት ወይም የቀረበውን ቅሬታ ለማስተናገድ ይችላል፡፡

፰/ የይግባኝ ሰሚው የባሕል ፍርድ ቤት የቀረበው ቅሬታ መጣራት እንዳለበት ካመነ መልስ ሰጪ እንዲገኝ መጥሪያ ያደርሰዋል፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት መልስ ሰጭ መጥሪያ ደርሶት የቀረ እንደሆነ በሌለበት ጉዳዩን አጣርቶ አስፈላጊውን ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## ፴፬. በባሕል ፍርድ ቤት የተሰጠውን እርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ስለማስፈፀም

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት ተከሳሽ ወይም ምስክር እንዲቀርብ ያስተላለፈውን ትዕዛዝ ወይም የተጠረጠረ ሰው ቀርቦ በመሐላ እንዲታመን የሚሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የቀረበለትን ጉዳይ ካጣራ በኋላ የሚሰጠውን ዕርቀ ውሳኔ በአካባቢ ባሕል ሕግ መሠረት ለማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡

፪/ በባሕል ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለመፈፀም ግዴታ ያለበት ሰው ቀርቦ እንዲፈጽም በባሕል ፍርድ ቤቱ ይታዘዛል፤ የባሕል ፍርድ ቤቱ የታዘዘው ሰው ለመፈፀም ፍላጎት እንደሌለው ከተረዳ፡-



5/ The Customary Court shall give a copy of its decision to a person requesting same within 15 days from the date the request is made.

6/ A party aggrieved by decision of Customary Court shall file his appeal to a body having jurisdiction within 30 days since taking copy of the decision.

7/ Notwithstanding the provisions of Sub-articles (4-6) of this Article, the Appeallate Customary Court or Wereda Court may give copy of the decision or accept an application for appeal without being bounded by the above time limit where it ascertains the existence of good cause.

8/ The Appeallate Customary Court may summon the defendant when it believes that there is an issue to be clarified.

9/ Where the defendant fails to appear after duly summoned in accordance with Sub-article (8) of this Article, it shall proceed to hear the appeal ex-parte and give judgement or order it deems appropriate.

## 34. Executing Judgement or Order Given by Customary Court

1/ Customary Court shall have the power to enforce the order it has given for appearance of a defendant or a witness, or order given for the suspect to appear and take oath as well as its judgement or order given in accordance with customary law of the area.

2/ A person bound to execute the decision or order of the Customary Court shall be ordered to appear and execute same; where the Customary Court understands that the person so has no will or interest to execute:

ሀ) ጠርቶ ምክንያቱን ይጠይቃል፤ እንዲፈፅም ያስጠነቅቃል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የማይቀበል ከሆነ እንደ ጉዳዩ ተጨባጭ ሁኔታ እና የባሕል ፍርድ ቤቱ በሚሠራበት አከባቢ ባለው የባሕል ሕግ መሠረት የኢኮኖሚ ወይም የማኅበራዊ ማዕቀብ ይጣልበታል ወይም የቀበሌ መስተዳደርን በማዘዝ ማስፈፀም ይችላል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እና (ለ) ባሉት የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለማስፈፀም ጥረት ተደርጎ ካልተቻለ የባሕል ፍርድ ቤቱ ማስፈጸም ያልቻለበትን ምክንያት በመጥቀስ እንዲያስፈፅም ለወረዳ ፍርድ ቤት ያሳውቃል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) መሠረት የቀረበለትን የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የወረዳው ፍርድ ቤት በራሱ እንደተሰጠ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ወስዶ ያስፈፅማል።

፫/ አንድ ወገን በተሰጠው የዕርቅ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ወደ የባሕል ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ጠይቆ ከሆነ ዕልባት እስኪሰጠው ድረስ አፈፃፀሙ በባሕል ሕግ መሠረት ታግዶ እንዲቆይ የባሕል ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## ስለ አማካሪ ምክር ቤት መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባር

### ፴፭. ስለ መቋቋም

፩/ በአማራ ክልል የባሕል ፍርድ ቤቶችን የሚያማክር የአማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለአማራ ክልል ምክር ቤት ይሆናል።



A) Summon and ask his reasons and give warn execute;

B) Where the person failed to comply wit warning given in accordance with Sub-arti (A) of this Article, he shall be imposed econ or social sanction in accordance with circumstance of the case and customary law o area or use the Kebele administration to exe its judgement;

C) Where the attempt to execute the judgemen order in accordance with Sub-article 2 (A ) and of this Article is failed, the Customary Court sh notify the reason why it failed to execute a request the wereda court to execute the judgeme

D) The Wereda Court shall execute the decisi referred from the Customary Court in accordan with Sub-article (2) (C) by considering as i decision.

3/ When one party takes appeal to an appellat customary court on judgement or order of given to him, the customary court may order the execution to be stayed until the case is resolved by the appellate court.

## PART SIX

## ESTABLISHMENT, STRUCTURE, POWER AND FUNCTION OF ADVISORY COUNCIL

### 35. Establishment

1/ An Advisory Council (here in after called the Council) is established by this proclamation to give advice for Customary Courts in the Amhara Region.

2/ The Advisory Council shall be accountable to the Amhara Region Council.

## ፴፮. የምክር ቤት አባላት

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

(ሀ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት.. ሰብሳቢ፤

(ለ) የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ኃላፊ........ምክትል ሰብሳቢ፤

(ሐ) የባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ.........ፀሐፊ፤

(መ) የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ..........................................አባል፤

(ሠ) የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር...................አባል፤

(ረ) የክልሉ የፍትሕና የሕግ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር..................................አባል፤

(ሰ) የክልሉ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዝዳንት......አባል፤

(ሸ) ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በሰብሳቢው አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚወሰኑ አባላት ይኖሩታል::

## ፴፯. የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩/ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል::

፪/ በስብሰባው ላይ ግማሽ የሚሆኑት የምክር ቤት አባላት ከተገኙ የስብሰባው ምልአተ ጉባዔ ይሆናል::

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ የሚጸድቅ ሲሆን የአባላት ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሐሳብ የምክር ቤቱ ውሳኔ ይሆናል::

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ሊወስን ይችላል::

## 36. Member of the Council

1/ The Council shall have the following members:

A) The Region Supreme Court President… Chairperson;

B) The Region Justice Bureau Head…Vice Chairperson;

C) Culture and Tourism Bureau Head……. Secretary;

D) Women's, Youth and Social Affairs Head…………………………………………………………Member;

E) The Regional Police Commissioner……. Member;

F) The Regional Justice and Law Institute Chief Director ……………………………….…. Member;

G) The Regional Bar Association President...Member;

H) Other stakeholders as proposed by the chairperson to be a member.

## 37. Meeting Procedure of the Council

1/ While the Council shall hold its regular meetings twice a year, the chairperson may call for an extraordinary meeting as necessary.

2/ It shall be quorum if half of the members are present in the meeting.

3/ While decision of the council shall be made by majority vote, the decision supported by the chairperson shall be final in case of tie.

4/ Without prejudice to Sub-articles (1-3) of this Article, the Council may issue its own internal governing directive of meeting procedures.

## ፴፰. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ የአዋጁን አጠቃላይ አፈፃፀም ይከታተላል፤ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ላይ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል፤

፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተለያየ ኃለፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ኃፊነታቸውን በአግባቡ ስለመተግበራቸው ይከታተላል፤ ያስተገብራል፤

፫/ የሰው ኃይልና ሎጂስቲክ እገዛ የሚደረግበት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ያስተገብራል፤

፬/ የብቃት ማነስ እና የሥነ ምግባር ጉድለት እንዳለባቸው የተረጋገጠ ሽማግሌዎችን ከሥራ ለማንሣት በባሕል ሕጉ መሠረት የሚሰጠውን ውሳኔ መርምሮ ያጸድቃል፤

፭/ የባሕል ፍርድ ቤቶች የሚቋቋሙበትን፣ እውቅና የሚያገኙበትን፣ የሚስፋፉበትን እና የሚደራጅበትን ስትራቴጂ ይዘረጋል፤

፮/ የባሕል ፍርድ ቤቶች በአገልግሎት አሰጣጥና በአፈፃፀም የሚገጥማቸውን ችግር እየተከታተለ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፯/ የባሕል ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን በየጊዜው በሚቀርብ ሪፖርት ይከታተላል፣ ምክረ-ሐሳብ ይሰጣል፤

፰/ ሽማግሌዎች በየጊዜው ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ስትራቴጂ ይነድፋል፤

፱. ምክር ቤቱ የራሱን የውስጥ የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል።



## 38. Powers and Duties of the Cou

The Council shall have the following powers a

1/ Monitors the overall implementation proclamation and provide recommendat corrective measures;

2/ Oversees the proper execution of duties assi various institutions under this proclamati coordinates same;

3/ Develops a system in which human resourc logistics support to be provided and ensures compliance;

4/ Investigates and approves decisions regardin remove elders from the Customary Court du their lack of capacity or ethical violations;

5/ Develops strategies to facilitate the establishme recognition, expansion, and organization Customary Courts;

6/ Monitors and provides support to address th challenges faced by Customary Courts in servic delivery and execution.

7/ Follows up the performance reports submitted by customary courts in accordance with this proclamation and offer recommendations.

8/ Devises a strategy in which elders to get trainings from time to time;

9/ The Council shall prepare its own internal working directives.

## ፴፱. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

፩/ ምክር ቤቱ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር የሚደራጅ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፪/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ በጀትና የሰው ኃይል ይመድባል፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የጽሕፈት ቤት አገልግሎት ይሰጣል፤ የእለት ተእለት ሥራዎችን ይመራል፤

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት ዝርዝር ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት በሚመድቡት ወኪል በኩል በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ለጽሕፈት ቤቱ የሚያቀርቡ ሲሆን ይህንን ሪፖርት ጽሕፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የሚያቀርብ ይሆናል፤

፭/ የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈፅማል፤ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፵. የገቢ ምንጭ

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፦

ሀ) በባሕል ፍርድ ቤቱ የሥልጣን ወሰን ውስጥ ከሚኖር ሕዝብ የሚሰበሰብ መዋጮ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፰ መሠረት የሚወሰን የገንዘብ ቅጣት፤

ሐ) መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የሚሰበሰብ ድጋፍ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ሁኔታ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡



## 39. Secretariat of the Council

1/ The Council shall have a secretariat to be organized under the Regional Supreme Court.

2/ The Regional Supreme Court shall allocate th necessary budget and human resources to th secretariat.

3/ The secretariat shall offer secretarial services to th Council and lead daily operations;

4/ In accordance with this proclamation, whi specifically responsible organs shall submit quarter reports through their representatives, the secreta shall also present this reports to the Council;

5/ Shall execute decisions and perform other duties assigned by the Council.

## PART SEVEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 40. Source of Income

1/ Customary court shall have the following sources income:

A) Contributions to be collected from lo community under jurisdiction of the custom court;

B) Fine to be decided pursuant to Article 48 of proclamation;

C) Financial support to be collected f government and non-governmental bodies.

2/ Particulars for the implementation of Sub-articl of this Article shall be determined by a regulatio be issued.

## ፵፩. የገቢ አጠቃቀም ሁኔታ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ መሠረት የሚሰባሰብ ገቢ ለሚከተሉት ዓላማዎች የሚውል ይሆናል:-

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፤

፪/ ለፀሐፊና ለሌሎች የባሕል ፍርድ ቤት ሠራተኞች በደንብ እና በመመርያ የሚወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞችና ክፍያዎችን ለመፈፀም::

## ፵፪. ተጠሪነት

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋም ወይም እውቅና የሚሰጠው የባሕል ፍርድ ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል::

## ፵፫. የፍርድ ቤቶች ግዴታ

፩/ ይህንን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል በሚወጡ ደንብና መመርያዎች የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል:-

ሀ) ጉዳዮች በባሕል ፍርድ ቤት እልባት እንዲያገኙ ያበረታታል፤

ለ) ሰብዓዊ መብት፣ የሥነ-ምግባር መርሆዎች እና አስፈላጊ በሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ለሽማግሌዎች ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሐ) ለክልሉ ምክር ቤት በሚያቀርበው የሥራ ክንውን ሪፖርት ውስጥ የባሕል ፍርድ ቤቶችን የሥራ ክንውንን ያካትታል፤

መ) ካለው የሰው ኃይልና ሎጂስቲክ እገዛ ያደርጋል፤

ሠ) ከወረዳው ፍርድ ቤት ጋር በመሆን የባሕል ፍርድ ቤቶችን ገቢ ለማሳዳግ የሚረዳ ገቢ (ድጋፍ) ይሰበስባል::

፪/ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል:-

ሀ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የባሕል ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤



## 41. Utilization of the Income

The income to be collected in accordance with A
40 of this Proclamation shall be used for the follo
purposes:

1/ To improve service delivery of the Customary C

2/ To effect payments and benefits of the Secretary
other employees of the Customary Court as ma
determined by a regulation and directive to be issu

## 42. Accountability

The Customary Court established or to be recogni
under this proclamation shall be accountable to
Regional Supreme Court.

## 43. Obligations of Courts

1/ Without prejudice to what may be determined by
regulation and directive to be issued, the Amha
Regional Supreme Court shall have the followi
obligations:

A) Encourages disputes to be resolved by Customar
Courts;

B) Provides training or facilitates for the provision o
trainings to the elders on human rights, ethica
values, and other relevant topics;

C) Incorporates reports about the customary court i
its report to present to the Region Council;

D) Provides human resource and logistic support if it
has;

E) Gathers income (financial support) helping to increase income of the customary courts in collaboration with wereda courts.

2/ Without prejudice to what may be determined by a regulation and directive to be issued to implement this proclamation, wereda Court shall have the following obligations:

A) Makes Customary Courts to be establish in accordance with provisions of this Proclamation;

ለ) ግጭቶችን ሲፈቱ ለቆዩ የማኅበረሰብ ተቋማት እንደ ባሕል ፍርድ ቤት እውቅና ይሰጣል፤ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

ሐ) ሽማግሌዎች እንዲመረጡ እና ፀሐፊ እንዲመደብ ያደርጋል፤

መ) የባሕል ፍርድ ቤቶችን ሥራ አፈፀፃም በማስመልከት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤ ይገመግማል፤ ውጤታማነታቸውን ለማሻሻል አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

ሠ) በባሕል ፍርድ ቤቶች የሚተላለፈውን የቅጣት አፈፃፀም ይከታተላል፣ ጉድለት ባለበት ቦታ አስፈላጊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ረ) በባሕል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፤ ድጋፍ እንዲያደርግ ሲጠየቅም ያስፈፅማል፡፡

## ፵፬. የቀበሌ አስተዳደር ግዴታ

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር በባሕል ፍርድ ቤት ሲጠየቅ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የባሕል ፍርድ ቤቱ የሚሰየምበትን ቦታ ደኅንነት ማስጠበቅ፤

፪/ የባሕል ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ መፈፀም ወይም ማስፈፀም፤

፫/ የገንዘብ ቅጣትንና የጉልበት ሥራን ማስፈፀም፤

፬/ የባሕላዊ ፍርድ የሚካሄድበትን ቦታ ማመቻቸት፡፡

## ፵፭. የባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ግዴታ

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ እና በየደረጃው የሚገኙ መዋቅሮቹ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-



B) Recognizes social organizations involved in dis resolution as Customary Courts and provide t with the necessary support;

C) Makes elders to be appointed and secretary to assigned;

D) Makes the submission reports regarding Custom Courts performance; evaluates; makes necess assistance to enhance their effectiveness;

E) Follows up the execution of penalties made customary courts and makes necessary correct actions to be taken in areas where gaps exist;

F) Follows up the execution of decisions made by customary courts and makes the execution up support request.

## 44. Obligation of Kebele Administration

Without prejudice to what may be determined by regulation and directive to be issued, the Kebe Administration shall have the following obligatio when requested by Customary Court:

1/ Ensuring the security of the Customary Court heari environment;

2/ Executing or causing the execution of orders give by Customary Court;

3/ Execution of fines and compulsory labor;

4/ Arranging a place where the Customary Court carri out its duties.

## 45. Obligation of Culture and Tourism Bureau

Without prejudice to what may be determined by regulation and directive to be issued, Culture an Tourism Bureau and its subordinates shall have th following obligations:

፩/ የባሕል ሕግ እንዲያድግ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ምርምሮችን በማካሄድ ውጤቱ ሥራ ላይ እንዲውል ይሠራል፤

፪/ የክልሉን የባሕል ሕጎች የኮዲፍኬሽን ሥራዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይሠራል፤

፫/ ሽማግሌዎች የባሕል ሕግ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬/ የባሕል ሕግ ከትውልድ ትውልድ እየተሻገረ እንዲሄድ አስፈላጊውን ሥራ ይሠራል፤

፭/ የባሕል ፍርድ ቤቶች እየተሻሻሉ እንዲሄዱ የሚያስችሉ የትኛውንም ሥራዎች ይሠራል።

## ፵፮. ድጋፍ የመስጠት ግዴታ

፩/ ማንኛውም የሚመለከተው አካል በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱትን ጉዳዮች ሥራ ላይ ለማዋል ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት።

፪/ ግለሰቦች፣ መረዳጃ እድሮች እንዲሁም መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በባሕል ፍርድ ቤት የተሰጡ የማዕቀብ ውሳኔዎችና ሌሎች ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለባቸው።

## ፵፯. ስለ ሽማግሌዎች ጉባዔ

፩/ የሽማግሌዎች ጉባዔ በወረዳ ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል።

፪/ የወረዳው የመጀመሪያ ደረጃና ይግባኝ ሰሚ የባሕል ፍርድ ቤት ሽማሌዎች በጉባዔው ላይ ይሳተፋሉ።

፫/ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት የጉባዔው ሰብሳቢ፣ የወረዳው የባሕል እና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ ይሆናሉ።

፬/ የጉባዔው ተሳታፊዎች ከጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በቀረቡ አጀንዳዎች ላይ ይወያያል።



1/ Works for implementation of findings by cond researches aimed at the development of custo courts in collaborating with other concerned bo

2/ Works with concerned bodies to realiz codification of customary laws of the region;

3/ Facilitates for access of trainings to elde customary laws;

4/ Undertakes necessary activities so that custo laws to transfer from generation to generation;

5/ Undertakes any activities that helps Custo Courts to be flourished.

## 46. Obligation to Give Support

1/ Any concerned body shall have an obligation to support in implementing matters covered unde proclamation.

2/ Individuals, community associations as wel governmental and non-governmental bodies are bound to respect decisions given by Custor Courts related to sanctions and other orders.

## 47. Plenum of Elders

1/ The plenum of elders shall be convened once a ye woreda level.

2/ Elders of First Instance Customary Court Appellate Customary Court shall take part at plenum.

3/ President of Wereda Court shall be Chairperson of Plenum; Head of the Wereda Culture and Tour Office shall be vice chairperson of the plenum.

4/ The plenum participants shall discuss on agen presented from the Chairperson and the Vi Chairperson.

፭/ ጉባዔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሠረት ሽማግሌዎችን ይመርጣል፤ የብቃት ማነስ እና የሥነ ምግባር ጉድለት እንዳለባቸው የተረጋገጠን ከሥራ ላይ ያነሣል፡፡

፮/ በክልል ደረጃ የሚደረግ የሽማግሌዎች ጉባዔን በሚመለከት ዝርዝር በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፵፰. ቅጣቶች

፩/ የባሕል ፍርድ ቤት የአከባቢውን ባሕላዊ የክርክር ሥነ ሥርዓት ሕግ የማያከብርን ሰው መቅጣት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ድርጊቶች በአካባቢው የባሕል ሕግ መሠረት ያሉትን ቅጣቶች የሚያስቀጡ ይሆናሉ፡-

ሀ) በባሕል ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሆኖ እንዲቀርብ መጥሪያ ደርሶት ያለ በቂ ምክንያት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ፤

ለ) የባሕል ፍርድ ቤቱ ሥራውን እያከናወነ ባለበት ጊዜ ያሳሳተ፣ የረበሸ ወይም ፍርድ ቤቱ ላይ ሽማግሌን፣ ፀሐፊን፣ ባለጉዳይን ወይም ምስክሮችን የሰደበ፣ የዛተባቸው፣ ያስፈራራ ወይም በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ሥራ ያስተጓጎለ፤

ሐ) የባሕል ፍርድ ቤት የትኛውም ትእዛዙን ያላከበረ ወይም ሥራው መሀል ጣልቃ በመግባት አላስፈላጊ ተፅእኖ የፈጠረ አካል ላይ በባሕል ሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## ፵፱. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የአማራ ክልል ምክር ቤት አዋጁን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

፪/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

5/ The Plenum shall elect elders in accordance with Article 11 of this Proclamation, and dismiss those having lack of capacity or ethical defects.

6/ Regarding to plenum of elders conducted at the regional level shall be determined by detailed directive to be issued.

## 48. Penalties

1/ Customary Court may penalize a person who fails to comply with customary law procedure of the area.

2/ Notwithstanding with the provision of Sub-article (1) of this Article, the following acts shall make penalized in accordance with customary law of the area.

A) Where a person failed to appear without good cause after being duly summoned to appear in customary court as a defendant;

B) A person who misleads, disturbs while the customary court is carrying out its duties; insults, threats or coerces elders, secretary, parties or witnesses at the customary court or delays proceeding in any condition;

C) Customary Court may take necessary measures against any-one who failed to obey its order or unnecessarily intervenes in its activities based on customary law.

## 49. Power to Issue Regulation and Directives

1/ The Amhara National Region Council may issue regulation needed to implement this Proclamation.

2/ The Amhara Regional Supreme Court may issue directive to implement this proclamation and regulation to be issued for the implementation of this proclamation.

## ፶. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአዋጁን ድንጋጌዎች የሚቃረን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ውሳኔ ተፈፃሚነት የለውም::

## ፶፩. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል::

ባሕር ዳር

ግንቦት ፳፱ ቀን 2017 ዓ/ም

አረጋ ከበደ ለጋስ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት



## 50. Inapplicable Laws

Any proclamation, regulation, directive or decisio inconsistent with this proclamation shall be inapplicab with respect to matters provided for in this Proclamatio

## 51. Effective Date

This proclamation shall come in to force from the date of its publication on the Regional Zikre Hig Gazette.

**Done at Bahir Dar,**

**This 6th Date of June/2025**

**Arega Kebede Legas**

**President of the Amhara National Regional State**